የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፳፰
አዲስ አበባ ጥር ፳ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No.28
ADDIS ABABA, 29th January, 2016

<u>ማውጫ</u>

አዋጅ ቁጥር ፱፻፳፩/፪ሺ፰ ዓ.ም

፪ሺ፰ በጀት አመት የፌደራል መንግሥት ተጨማሪ በጀት አዋጅ..................................................ገፅ ፰ሺ፯፻፶፮
ሠንጠረዥ...............................................ገፅ ፰ሺ፯፻፶፰

**CONTENTS**

Proclamation No. 921/2016

2008 (E.C) Fiscal Year Federal Government Supplementary Budget Proclamation ………………………page 8756
Schedule………………………………………page 8758

## አዋጅ ቁጥር ፱፻፳፩/፪ሺ፰

## <u>የፌዴራል መንግሥት የተጨማሪ በጀት አዋጅ</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና(፲፩) እንዲሁም በኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፰/፪ሺ፩ አንቀጽ ፳፯ መሠረት ለተጨማሪ መደበኛና ካፒታል ሥራዎች የሚከተለው ታውጇል፡፡

አንቀጽ ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "፪ሺ፰ በጀት አመት የፌደራል መንግሥት ተጨማሪ በጀት አዋጅ ቁጥር ፱፻፳፩/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

አንቀጽ ፪. <u>ተጨማሪ በጀት</u>

ከሐምሌ ፩ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም በሚፈጸመው በአንድ የበጀት አመት ጊዜ ውስጥ በፌደራል መንግሥት ከሚገኘው ገቢ ላይ ከዚህ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ውስጥ ለተጠቀሱት ሥራዎችና አገልግሎቶች ቀጥሎ እንደተመለከተው፡-

## PROCLAMATION No. 921 /2016

## <u>A SUPPLEMENTARY BUDGET PROCLAMATION FOR FEDERAL GOVERNMENT UNDERTAKINGS</u>

In accordance with Article 55(1) and (11) of the Constitution of the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and in accordance with Article 27 of the Federal Government of Ethiopia Financial Administration Proclamation No. 648/2009 a supplementary of Recurrent budget and Capital Budget is hereby proclaimed as follows:

Article 1. **<u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "2008(E.C) Fiscal Year Federal Government Supplementary Budget Proclamation No.921/2016".

Article 2. **<u>Suplementary Budget</u>**

There is hereby appropriated a Supplementary Budget to the Federal Government, for the Fiscal Year commencing on Hamle 1, 2007 E.C. and ending on Sene 30, 2008 E.C. from Federal Government Domestic revenue:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

ሀ) ለመደበኛ ወጪዎች ብር 14,780,000,000

ለ/ ለካ□ታል □ጪዎች ብር 3,220,000,000

ጠቅላላ ድምር ብር 18,000,000,000

/አስራ ስምንት ቢሊዮን ብር/ በተጨማሪ ወጪ ሆኖ በፌደራሉ መንግሥት እንዲከፈል በዚህ የተጨማሪ በጀት አዋጅ ተፈቅዷል።

አንቀጽ ፫. የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ስልጣን

ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት የበላይ ኃላፊዎች ለየመሥሪያቤቶቻቸው ሥራና አገልግሎት ከፌደራል መንግሥት ገቢ በዚህ አዋጅ ለተጨማሪ ሥራዎች የተፈቀደላቸውን ተጨማሪ በጀት በሚጠይቁበት ጊዜ የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስትሩ እንዲከፍል ተፈቅዶለት ታዟል።

አንቀጽ ፬. የበጀቱ አጠቃቀም

በዚህ አዋጅ የተፈቀደው የተጨማሪ በጀት በ፪ሺ፰ በጀት ዓመት የበጀት አዋጅ ቁጥር ፱፻፲/፪ሺ፯ በተመለከተው መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፳ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

a) For Recurrent Expenditures Birr… ………………………… 14,780,000,000

b) For Capital Expenditures Birr ………………………… 3,220,000,000

Grand Total Birr 18,000,000,000

/Eighteen Billion Birr/ as set forth a schedule attached hereto.

**Article 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation**

The Minister of Finance and Economic Cooperation is hereby authorized and directed upon the request of the heads of the concerned government organs, to disburse out of the Federal Government revenues the additional amount appropriated herein for the undertakings of their respective organs.

Article 4. **Utilization of the Supplementary Budget**

Utilization of the Supplementary Budget shall be made in accordance with the Budget Proclamation No. 910/2015.

**Done at Addis Ababa, this 29th day of January 2016.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**